ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ
Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity
Efdpu@aol.com www.Finote.org

**በፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ**

**መጋቢት 9ቀን 2011 ዓም የተላለፈ ሐተታ**

## ብኩርናን በጭብጥ ምስር ያለወጠ !

## በጠላት ድግስ ገብቶ ያልቀላወጠ !

ያ የትላንትናው ጀግና ትውልድ ፤ የሀገሩን አኩሪ ታሪክ አክብሮ ያስከበረ ፤ ውርደትን ተፀይፎ፤ ለአምባግነን ሥርዓት ያልተንበረከከ፤ ለውጭ ጠላቶች ያልተበገረ መሆኑን ፤ በትግል ያስመሰከረ ትውልድ ነው ። ያዚያ ትውልድ አባላት የተሰባሰቡት በኢትዮጵያውያንነታቸው ብቻ ነበር ። ከልዩ ልዩ ብሄራትና ዕምነቶች የፈለቁ መሆናቸውን ቢገነዘቡትም ፤ ሁሉንም አሰባስቦ ለትግል ያሰለፋቸው ዕምነት ግን ኢትዮጵያዊነታቸው **ብቻ** እንደነሆነ ፤ ሁሉም ዜጋ የሚያውቀውና የተረዳው ነበር። ሀገራቸው፤ በብሄራት የታደለች ሀገር መሆኗን በመንገንዘባቸው ሁሉም ዜጎች በእኩልነትና በአንድነት ተባብረው መኖር እንደለባቸው አስቀድሞ ያመነበት ራዕይ ነበር። ያ ትውልድ፤ ዘውግንና ዜግነትን በሚዛን አስገብቶ በመታገሉ አኩሪ ታሪክን አስመዝግቦ አልፏል ።

ይህንን ሚዛን የማስጠበቅ ዕይታው ፤ ማነኛውም አክራሪና ጽንፈኛ አመለካከት እንዳይቆጠቁጥ የተቻለውን ሁሉ ፈጽሟል። ይኸንን በማድረጉም፤ ጣምራ ጠላቶችን አትርፏል። እነኘኸም፤ በአንድ በኩል ፤ አክራሪ ዘውገውኞች ሲሆኑ በሌላ በኩል ደግሞ ፤ የኢትዮጵያን ነፃናትና የዜጎቿን አንድነት ማየት የማይፈልጉ ባዕዳን ጠላቶቿ ነበሩ። ሁለቱንም እንዳመጣጣቸው ሲከላከል አይከፍሉ ዋጋ ከፍሏል። አይከፍሉ ዋጋ ቢከፍልም፤ የተሰዋላትን ሀገር ለማየት ግን አልታደለም ! እስካሁን !

የዛሪይቷ ኢትዮጵያ ፤ ፅንፈኛ ዘውገኞች የገነኑባት፤ ዜጎች ግን የከሰሙባት፤ ሀገር ሆናለች። ሀገሪቱን ጨፍልቆ፤ ነዋሪዎቿን በውዞና አማሰቃቅሎ ፤ ጥንታውያን ዕሴቶቿን አጥፍቶ፤ ታሪኳን አፍልሶ፤ የዚያን ጅግና ትውልድ ታሪክ አራክሶና የፈጸመውን መሥዋዕት እያጥላሉ የአዲስ ሀገር የመፍጠር ሙከራ ሴካታማ ሊሆን አይችልም። ያ ጀግና ትውልድ ከራሱ ህይወትና የግል ጥቅም በላይ ያስቀደመው ለሀገሩና ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃናትና ብልጽግና ነበር። አሁን በሥልጣን ላይ የሚገኙት ሰዎች ግን ይኸንን የታሪክ ሃቅ ሊቀበሉት አልፈለጉም።

የሀገሪቱ ታሪክ በእነርሱ እንደተጀመረ በመቁጠር፤ ብዥታ ውስጥ ገብተዋል። ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ፤ የዚያን ትውልድ ታሪክ በማጸልመት ሂደት ላይ ይገኛሉ ። የማጥላላት አነጋገራቸውን ስናዳምጠው፤

ምናልባት የአፍ ወለምታ ሊሆን ይችላል በማለት በቸልታ ለማለፍ ተሞክሮ ነበር። " **የአፍ ወለምታ በቅቤ አይታሽም;** " በሚል ይትበሃል፤ እያተዘብን ማለፍን መርጥን ነበር። ግን አድብ ሊገዙ አልፈለጉም። አሁንም ደጋግመው ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ የዚያን ሀገር ወዳድ ትውልድ መሥዋዕትነት ማጥላላቱን ቀጥለውበታል። ያዚያን ታሪካዊ ትግል፤ **የልዩነት ነጥብ፤ ግዝፈትና የመርኅ ልዩነት ፤ የፊደል አፃፃፍ ልዩነት** አድርጎ በመቁጠር **በ ሽ ና በ ቸ (እናሽንፋለን እና እናቸንፋለን** ) ልዩነት ምክንያት እርስ በእርሳቸው ተገዳደሉ፤ ተጠፋፉ ፤ ተጨራረሱ በሚል የጥላቻ ማዕበል ውስጥ በመግባት፤ ራሳቸው ተወናብደው አዲሱንም ትውልድ ጭምር ለማወናበድ በመድከም ላይ ናቸው።

ድካማቸው ውጤት እንደማያስገኝላቸው ብንገንዝብም ፤ድርጊታቸው ግን በሁለት ዐብይት ምክንያቶች ሊወገዝ ይገበዋል ብለን እናምናለን ። **አንደኛው** ምክንያት የፈጠራ ወሬ መሆኑ ሲሆን ፤ **ሁለተኛው** ምክንያት ደግሞ ፤ አዲሱ ትውልድ ዕውነተኛውን ታሪክ እንዳያውቅ የሚያደረግ መሰሪ ተልዕኮ ነው። ሁለቱም ምክንያቶች በታሪክና በሀገር ደረጃ ተቀባይነትን አያገኙም። የአሁኖቹ መሪዎች ይኽንን አስወቃሽና አስነዋሪ ድርጊት ለምን እንዳሚደጋግሙት፤ አስተዋይ ኅሊና ላለው ዜጋ ለመስማት የከብደዋል።

ምናልባት አዲሱ ትውልድ ፤ታሪካዊ ዕይታ ሊኖረው ይገባል ከሚል ግንዛቤ ብቻ፤ የ **ቸ** ንና የ **ሽ**ን ጉዳይ ዕውነተኛው ሀኔታ መግለፅ ካስፈለገ፤ ትክክለኛው ስዕል ማሳየት ይገባል፡-

**1ኛ.** ያ ትወልድ የነበረው ልዩነት የመሠረታዊ አቋም አለመጣጣም ነበር ። ይኸውም፡----

ደርግ የለውጡ መሪ ነው ሂሳዊ ድጋፍ እየሰጠን በስልጣን ላይ እንዲቆይ እናድርገው የሚሉ እንደ መኢሶን ያሉ ክፍሎች ባንድ በኩል የቆሙበት የለም ሥልጣን በሕዝብ እጅ መግባት አለበት በማለት ትግል ያካሄዱ እንደ ኢህአፓ ዓይነት ድርጅቶች በሌላ ወገን ሆነው የተሰለፉበት ረድፍ ነበር።

**2ኛ.** የየካቲቱ 66 ዓም ዐብዮት በጊዚያዊ የሽግግር ሂደት ማለፍ ስለሚገባው፤ የሽግግር መንግሥት ፤ ከሁሉም የኅበረተሰብ ክፍሎች በተወከሉ የሕዝብ እንደራሴዎችና ከወታደሩም ክፍል ጭምር ፤ የተወከሉ ያሉበት በተቋቋመ ጊዚያዊ ሕዝባዊ ሽግግር መንግሥት መኖር ይገባል የሚለውን የብዙሃን አመልካከት እንደ ኢሕአፓ የመሳሰሉ ድርጅቶች ደግፈው ሲቆሙ በሌላ በኩል ደግሞ ይ ጊዜያዊ ወታደራዊ ደርግ ለውጡን ሊመራ ይችላል በማለት የጊዚያዊ ሕዝባዊ መንግስትን ጥያቄ በሚቃወሙ የደርግ ተባባሪዎች መካከል የነበረ የልዩነት አቋም ነበረ። ይኽ ደግሞ፤ መሠረታዊ የሆነ የፖለቲካ ልዩነት ነው።

እነኝ ሁለት ልዩነቶች ፤ የመተከልና የአቋም ልዩነቶች ነበሩ/ ናቸው ። ስትራተጂያዊና የትግል ስልት ልዩነቶች ነበሩ/ ናቸው።

በአብዛኛው አመለካከት የኢትዮጵያ ታሪክ፤ ብዙ ውጣ- ውረድና ዕንቆቅልሽ የመላበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ አሁንም ከአምሳ ዐመቶች በኋላ፤ ሀገራችን በተመሳሳይ ሂደት ወስጥ ትገኛለች።

ዛሬም፤ እንደትላንቱ መራራ የሕዝብ ትግል በስገኘው ድል፤ ኢትዮጵያ በለውጥ ሽሽግግር ሂደት ትገኛለች ። መሠረታዊ ለውጥ እንደሚያስፈልጋትም ሁሉ ዜጋ ይጠብቃል ። መሠረታዊ ለውጥ ለማምጣት ደግሞ ፤

ስትራተጂያዊ አመለካከትና ሀገራዊ -ዴሞክራሲያዊ- ተቋማትን መግንባት ወሳኝነት አላቸው። የእነኝኽ ወሳኝ ጥያቄዎች አፍጥጦና አግጥቶ መምጣት ፤የኢሕዴግ መሪዎች አጣዳፊ ተግባር መሆኑን ሊገነዘቡት ይገባ ነበር ። ይኽንን መገንዘብ፤ የሀገሪቱን ሠላማዊና መረጋጋትን ለማስፈን በሚደረገው ሂደት የበኩሉን አስተዋፃኦ ያበረክታል። ከሁሉ በፊት ሊታሰብበት ይገባል ተብሎ የሚታመነው፤ የሀገሪቱ እንደ ሀገር የመቀጠልና የዜጎችኗ ሠላምና ደኅንነት ጉዳይ ነው።

የሀገር ኅልውናም ሆነ የዜጎቿ ሠላምና አንደነት ጉዳይ ለድርድር ቀርቶ ጥያቄ ውስጥ እንኳ ሊገባ እንዳማይችል መገንዘብ ብለኅነት ነው። ። መሠረታዊ-ዴሞክራሲያዊ -ሀገራዊ ተቋማትን መመስረት ይዋል- ይደር የሚባልበት ጉዳይ አይደለም ። እነኝህን ተግባራት ለማከናዋን ፤ ብልኅነትን፤ አስተዋይነትን፤ አርቆ መመልከትን ይጠይቃል። ሕዝቡን በኢትዮጵያዊነት አመለካከት እያሰባሰቡ ማሳተፍን ይጠይቃል።

ሠላማዊው የሽግግር ሂደት የታሰበውን ግብ እንዲመታ ከተፈለገ፤ በግድ የሕዝብ ሙሉ ተሳትፎ መኖሩን ማረጋገጥ ተገቢ ይሆናል። እኛ ብቻ እናውቅልሀለን የሚለው አባዜ፤ ያረጀ-ያፈጀ- ፤ ኋላ-ቀርና ጎታች መሆኑን መረዳት ይገባል። በሽግግር ለውጥ ሂደት ውስጥ፤ ሁለት ተፃፃሪ ኃይሎች ተፋጥጠው እንደሚቆሙ የታሪክ ሃቅ ነው። ለውጥ ፈላጊውና ለውጥ -አጋቹ በአጥፊና- ጠፊ ጎራ ስለሚሰለፉ፤ ለሀገር ጥፋትና ለሀብት ወድመት እንዲሁም ለሕዝብ መበታተን የሚያስከትሉት ጥፋት በቀላሉ ሊታይ አይገባውም::

አሁን በሀገሪቱ ያለው ነብራዊ ሁኔታ ይህንን ስጋት ጉልቶ በማሳያት ላይ ይገኛል። በሀገሪቱ ላይ የሚያንዣብበውን አደጋ ይበልጥ አስፈሪ የሚያደርገው በሚከተሉት ዕውነታዎች ይመስላሉ። እነርሱም፡-

**1ኛ.** እጅግ ከቁጥጥር ውጭ የሆነ የጦር መሳሪያ የሀገሪቱን ኬላዎች እየጣሰ ወደ ኢትዮጵያ እየገባ ነው። ልዩ ልዩ ዐላማ ያላቸው ቡድኖች የጦር መሳሪያውን በእጃቸው አስገብተዋል። ሠራዊቶቻቸውም እስከ አፍንጫቸው ታጥቀዋል። ሀገሪቱን የሚቆጣጠሩት የኢሕዴግ መሪዎች እነኝህን ታጣቂ ኃይሎች መቆጣጠር ይቅርና መጠናቸውን፤ ዓላማቸውንና እንቅስቃሴያቸውን እንኳ በተገቢ መንገድ የሚያውቃቸው አይመስልም። ብዙዎቹም የየራሳቸው ጦር ሠፈርና ቀጠናዎች አሏቸው ። ሠላማዊውን ሕዝብ ከቦታው የማፈናቅልና ሀብት የመዝረፍ ወንጀል ሲፈጽሙ ወደ ህግ ሊያቀርባቸው የሚችል የህግ ሥልጣን ያለው መንግሥታዊ አካል የለም ። ብዙዎቹ ዜጎች ፤ ኢትዮጵያ ወደ ዘመነ መሳፍንት አገዛዝ ቀስ በቀስ እየተሽጋገረች እንደ ሆነ ስጋታቸውን ይገልፃሉ ።

**2ኛ.** ሀገሪቱ አሁን የገጠማትን የኅልውና አደጋ፤ የበልጡኑ ለማባባስ ተግተው የሚሰሩ ኃይሎች በውጭና በሀገር ቤት ተሰልፈዋል። ለሕዝብ- ተሟጋቾች ነን ባይች - ነገረ-ፈጆች፤ አክቲቪስቶች፤ የማኅበራዊ ድረ-ገጽ ተዋናዮች፤ የሶሻል ሚዲያ አካኪ ዘረፉ- ባዮች፤ በሬ ወለደ፤ ሰማይ ታረሰ፤ የሚሉ ፕሮፓጋንዲስቶች ፤ በመተባበር የህዝቡን ሠላማዊ ኑሮ ቀውስ ውስጥ በማስገባት ላይ ናቸው ። ከላይ በተራ ቁጥር አንድ ከተዘረዘሩት ታጣቂ ኃይሎች ጋር በመተባበር ይሰራሉ ። የሁለቱም ኣላማ፤ ለረዥም ዓመታት ሲያልሙት የኖሩበትን ምኞት ለማሳካት እንደሆነ ይገመታል።

**3ኛ.** በተራ ቁጥር አንድ እና ሁለት የተዘረዘሩት ክፍሎች በተለያየ መንገድ የሚረዳቸው፤ የሚያዝዛቸውና የተለያዩ መመሪያዎችን በመስጠት የሚያሽከረክራቸው የውጭ ባዕዳን ኃይል እንዳላቸው መረዳት ከባድ

አልሆነም። የእነኝህ ሁሉ ድምር -ውጤት ፤ አሁን አዲስ አበባ ላይ በሥልጣን ለሚገኘው የኢሕዴን ቡድን ፤ የቱን ይኽል ከባድ እንደሚሆንበት መገመት አስቸጋሪ ሊሆን አይችልም ።

እንዲያውም ፤ ይኽንን ተጨማሪ ችግር ለመቋቋም ቀርቶ፤ ነባሩንና የደለበውን ሀገራዊ ችግር በሂደት ለመፍታት እንኳን ቀላል እንደማይሆን ኃላፊነት የሚሰማው ዜጋ ሁሉ የሚስተው አይሆንም። ታዲያ፤ በየትኛውም ቅርጽና ይዘት የመጣ ቡድን፤ ምንም እንኳ መንግሥታዊ ሥልጣን ቢይዝና የቱንም ያኀል ወታደራዊ አቅም ቢይዝም፤ ሕዝብን የሚያሳትፍ ሂደት ካልጀመረ ፤ ተልፍስፍሶ ይቀራታል እንጅ ፤ ፋይዳ ያለው ውጤት ማስመዘግብ አይሆንለትም። በሽግግር ሂደት፤ ሁሉም ዋነተኛ ተሳታፊ በመሆን ዋኝቶ የሚሻገርበት ዕድል ማገኘት ይኖርበታል ሲባል ፤ አንዱ አሸጋሪና ሌላው ተሻጋሪ የሚለው አረዳድ በሁሉም ዘንድ ተቀባይነቱ አያገኝም። ምክንያቱም፤ ለሁሉም ተደራሽ ሊሆን ስለማይችል ነው። ለዚኽም ነው፤ ሁሉም ባለድርሻ፤ መሳተፍ የሚኖርበት።

ለአለፉት አምሣና አርባ ዐመታት፤ በትግል ሰፊና ጥልቅ ተመክሮን ያከበተው ትውልድ በዚህ ሂደት ውስጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊኖረው እንደሚችል አከራካሪ አይደለም። ሌላው ይቅርና ያ ትውልድ፤ በታሪክ ሲገመገምና ሲፈረድ፤ የሚከተልቱትን መሠረታዊ ዕሴቶችን አንግቦ ኖሯል። እነርሱን አንግቦ መቆየቱ ፤ አሁን ለአለው ሁኔታ ተፈልጎ የማይገኝና ብርቅየ ኃይል መሆኑን ያረጋግጥለታል።

ያ ሀገር ወዳድና ጀግና ትውልድ ፤ በሚከተሉት ምንነቱና ማንነቱ በሕዝብ ይታወቃል።

**1ኛ.** በስብዕናው፤ በሞራል ልዕልናው ፤ በሀገር ታማኝነቱና በሕዝባዊ ፍቅሩ፤

**2ኛ.** በዓላማ ፅናቱ፤ በአይበገሬነቱና ለውጭ ኃይሎችም ሆነ ለሀገር ውስጥ አባገነኖች ተንበርካኪ አለመሆኑ፤

**3ኛ.** ለአላፊ ጠፊ ቁሳቁስም ሆነ፤ ለሥልጣን ጥቅም የማያሸረግድ፤ የማይንበረከክ ፤ መሆኑ፤

**4ኛ.** በሀገር ሉዓላዊነትም ሆነ በሕዝብ አንደንትና ነፃነት የማይደራደር መሆኑን ያስመሰከረ፤

**5ኛ.** ሀገሩንና ሕዝቡን በክፉ ቀናቸው አኃልጦ፤ ከድቶና ተርበትብቶ ያልሸሻቸው፤ያልከዳቸው፤ መሆኑ፤

**6ኛ.** ተነሳሽነቱ፤ አፍላቂነቱ፤ ወጥነቱ ፤ ስትራተጂያዊ አመለካከቱና ዴሞክራሲያዊ ራዕዩ፤ ዘመን ተሻጋሪ ና ፤ ለመጭው ትውልድ እሴቱን አሸጋሪ መሆኑ፤ ከብዙዎቹ ባህርያቱ መካከል ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

ታሪክ ማለት በአውንታዊም ሆነ በአሉታዊ ገፅታው የትውልዶች ቅብብሎሽ እንደመሆኑ መጠን፤ የነበረውን ትውልድ ከተተኪው ትውልድ ጋር እያዛመዱና እየስተባበሩ ለሀገር ዕድገትና ለሕዝብ ጥቅም ማዘጋጀት ፤ የማይቋረጥ ሂደት መሆኑ ሊዘነጋ አይገባውም ። ነባሩን እያጠፉ፤አዲሱን ማጎልመስና ማጠንከር አይቻልም ። የኀብረተስብ ታሪክም ይኽንን የሚደግፍ አይምስልም ።

አኩሪ ታሪክ የሰራ ትውልድ፤ ለታሪኩና ለኢትዮጵያዊ ማነነቱ ቀናዒ ነው። ይኸም ባኅርዩ፤ ለሀገሩና ለሚታገልለት ሕዝብ ጥቅምና ክብር ቀናዒ ያደርገዋል። በየመድረኩ የዚያን ጀግና ትውልድ ታሪክ ለማጠልሸት የሚፍጨረጨሩት ክፍሎች ከድርጊታቸው እንዲቆጠቡ እያሳሰብን የሚቀጥሉበት ከሆነ ግን በድርጊታቸው የሚያፍሩበት ጊዜ ይመጣል እንላለን።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኖራለች !